# የአባይ ጸሃዬ ጦርነት በሚለው ላይ ─ ምላሽ ለተስፋዬ ገብረአብ

ግርማ ካሳ

January 29, 2016

አቶ ተስፋዬ ገበረአብ አንድ ወቅት የኢሕአዴግ ባለስልጣን የነበሩ ሰው ናቸው። ጥሩ ጸሃፊ ናቸው። ከኦሮሞ ብሄረተኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው። አንድ ወቅት እንደዉም የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር ላይ የክብር እንግዳ ሆኖ ቀርበው ነበር። በዚይን ወቅት "በሞጋሳ እኔም ኦሮሞ ነኝ" ብለው ነበር። ሞጋሳ አንድ ሰው "ኦሮሞ"ባይሆንም የኦሮሞን ባህልንና ቋንቋን ከተቀበለ፣ በኦሮሞ "ሽማግሌዎች" ፍቃድ "ኦሮሞ" የሚሆንብት ስርዓት ነው።(naturalized ኦሮሞነት)

አቶ ተስፋዬ "የአባይ ጸሐዬ ጦርነት" በሚል ርእስ አንድ ጽሁፍ አስነብበዉናል። በጽሁፉ እነ አባይ ጸሃዬ አማራውን እና ኦሮሞውን በማጣላት በስልጣን ለመቆየት የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ነው የገለጹት። "ከመነሻው በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፌደራል ስርአት ለመጠቀም ሲነሱ በህዝቦች መካከል በሚፈጠር አለመግባባትስልጣናቸውን ለማቆየት እንደሚችሉ በማመን ነበር። በርግጥም ተጠቅመውበታል" ሲሉ ፣ በስልጣን ለመቆየት ሲባል ህዝብን በዘር ለመከፋፈል ከጠዋቱ ከጅምሩ የሕወሃት አጀንዳ እንደነበረ ነው በጥሩ ቃላቶች የተነተኑልን።

እዚህ ላይ ከአቶ ተስፋዬ ገብረአብ ጋር በጣም እስማማለሁ። በርግጥም በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የፌዴራል ስርዓት ዋና አላማ፣ የብሄረሰቦችን መብት ለማስጠበቅ ታስቦ ሳይሆን በሕዝብና በሕዝብ መካከል ግድግዳን በመፍጠር ከፋፍሎ ለመግዛት እንደሆነ ብዙዎቻችን ደጋግምመን ስንጽፍፍበትና ስንናገረው የነበረ ጉዳይ ነው።

በነገራችን ላይ አቶ ተስፋዬ ራሳቸው የሕወሃት ባለስልጣን በነበሩበት ጊዜ የዚህ በዘር የመከፋፈል እንቅስቃሴ አካል እንደነበሩ መረሳት የለበትም። በተለይም የቡርቃ ዝምታ በሚል ርእስ የጻፉት፣ በፈጠራ ላይ የተመረኮዘ መጽሐፍ ፣ ሆን ተብሎ በኦሮሞዎችን እና በሌላው ማህበረሰብ መካከል ትልቅ ጥላቻ እንዲኖር ያደረገ፣ በጣምመርዛማ መጽሐፍ ነበር። ታዲያ አሁን አቶ ተስፋዬ፣ ከወያኔዎች ጋር ሲጣላ፣ ዞር ብሎ ስለ ወያኔ ዘረኘነት ሲነግረን ማየት ትንሽ ያስቃል። ለምንኛውም፣ ግድ የለም፣ ምናልባት የአመለካከት ለውጥ ተፈጥሮ ሊሆን ስለሚችል፣  የቡርቃ ዝማትን ለጊዜው ትቼ ወደሌሎች ነጥቦች እሄዳለሁ።

አቶ ተስፋየ ለመግለጽ እንደሞከሩት፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለመለያየት ሆን ተብሎ ከመነሻው የተዘረጋው፣ በኦነግና በሕወሃት ተግባራዊ የሆነውና በሕዝቡ ላይ በኃይል የተጫነው በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የፌዴራል ስርዓት፣  አንዱ ዉጤት "ኦሮሚያ" የምትባል ክልል መፈጠሯ ነው። ከዚያ በፊት ኦሮሚያ የምትባል ክፍለ ሃገር፣ ዞን፣ ወረዳመንደር ኖራ አታውቅም። ኦነግን የመንግስት አካል ለማድረግ ሲባል ብቻ የተፈጠረች ክልል ናት። ይች ክልል ፣ ለአስተድደር አመች ካለመሆኗ የተነሳ ለብዙ ግጭቶችና አለመስምማቶች ምክንያት ሆናለች።

ኦሮሚያን ጨመሮ አሁን ያሉት ዘረኛው የፌዴራል አወቃቀር የወለዳቸው ክልሎች፣ አሁን እንዳለው ቋንቋን ብቻ ሳይሆን፣ የአስተዳደር አመችነትን፣ የሕዝብ አሰፋፈርን፣ ባህልን፣ የህዝቡ ፍላጎትን፣ ኢኮኖሚን፣ ጂዮግራፊን ...ባካተተ መልኩ በጥናት፣ መስተካከል እንዳለባቸው የብዙዎች እምነት ነው።

አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ግን፣ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ለከፋፍለህ ግዛ ከመነሻው የተጠቀመብት የፌዴራል ስርዓት እንደሆነ ግሩም በሆነ ሁኔታ በሳፈሩበት ብእራቸው፣ ወረድ ብለው ደግሞ፣  "የአማራ ልሂቃን ቢያንስ ኦሮሚያን እንደ ክልል በማወቅ የመቀራረቡን መንገድ መክፈት ይጠበቅባቸዋል" ሲሉ በኦነግና በሕወሃት በሃይል በሕዝቡ ላይየተጫኘነን ፌዴራሊዝም መቀበል እንደሚገባ ይነግሩናል። በቀኝ እጅ የተገነባን በግራ እጅ ማፍረስ ይሉታል ይሄ ነው።

ሌሎች ብዙ አቶ ተስፋዬ ጫር ጫር ያደረጓቸው ነጥቦች አሉ። በተለይም "አማራ" ስላሉት ማህበረሰብ የጻፋቸው ትንሽ መስመር የለቀቁ አባባሎችን አንብቢያለሁ። ብዙም እዚያ ላይ አሁን ለጊዜው አላጠፋም። ግን ሳልጠቅስ የማላልፈው አንድ ነጥብ አለ።

በኦሮሚያ የተነሳውን ተቃዉሞ በመደገፍ፣ በኦሮሚያ ባሉ ትላልቅ ከተሞችና በሌሎች ክልሎች ያለው ማህበረሰብ ተነስቷል ማለት አይቻልም። ይሄም የራሱ የሆነ ምክንያቶች አሉት። ዶር መሳይ ከበደ እንደጻፉት ላለፉት 25 በነበረው ሁኔታ ጥርጣሬ መኖሩ (ብዙዎች በኦሮሞ አክራሪዎች ጥቃት ሲፈጸምባቸው፣ ከቅያቸው ሲባረሩስለነበረ ...) አንድ ምክንያት ነው። ሕዝቡ አለመደራጀቱ፣ የኦሮሞ ተቃውዋሚዎች ይዘዉት የነበረው አጀንዳ አገር አቀፍ አለመሆኑ እንደ ሌሎች አበይት ምክንያቶች ሊጠቀሱ  የሚችሉ ናቸው። ሆኖም አቶ ተስፋዬ ገብረዓብ፣ ምክንያቶችን ከመረዳት ይልክ፣ የኦሮሞዎችን ተቃዉሞ አልደገፉም በሚል፣ ለሌላው ማህበረሰብማስጠንቀቂያ ቢጤም ለመስጠት የሞከሩበት ሁኔታ ነው ያለው።

"በቅርቡ የወያኔ ነባር አባል ከሆነ የቀድሞ ወዳጄ ጋር በፅሁፍ ስናወጋ" ያለው ተስፋዬ፣ ይሄ ወዳጁ "የሞጋሳ ዘመዶችህ (ኦሮሞዎች ማለቱ ነው) አይሳካላቸውም። አማሮች ለታክቲክም ቢሆን ከኛ ጋር ናቸው።" እንዳቸው ጽፈዋል። ሌላም ማህበረሰብ ከወያኔዎች ጎን እንደቆመ ነው ሊያመላክቱን የሞከሩት። ይሄም አንድ ማህበረሰብ ዝምአለ ማለት አገዛዙን ደገፈ ወደ ማለት ድምዳሜ እንደመድረስ ነው። በአዲስ አበባ ከ 200 በላይ ዜጎች ሲረግፉ ሌሎች አልተነሱም ነበር። ያ ማለት የባህር ዳር፣ የደሴ፣ የአዳማ፣ የአዋሳ፣ የአምቦ ህዝብ ከወያኔዎች ጋር ቆሞ ነበር እንደማለት ነው።

ወረድ ብለዉም አቶ ተስፋዬ " የኦሮሞ ህዝብ አመፁን አጠናክሮ ቀጥሎ ብቻውን የወያኔን ስርአት ለማስወገድ ከበቃ ለሌላው ወገን ለፀፀት የሚያበቃ ታሪካዊ ስህተት ይሆንበታል። በአብሮ መኖር ሂደት ሌሎች የሚሉትን መስማት ቀዳሚ ጉዳይ ነው።

የኦሮሚያን አመፅ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም እንዲሳተፉበት ሲጠየቁ፤ ለነገ አብሮነትበማሰብ እንጂ የኦሮሞ ህዝብ ብቻውን ወያኔን ማንበርከክ አይችልም ከሚል አልነበረም። ይህን አብሮ የመታገል ጥያቄ በተሳሳተ መንገድ የተገነዘቡ ወገኖች ወያኔን ስልጣን ላይ በማቆየቱ ረገድ የማይናቅ ድርሻ እያበረከቱ ነው" ሲልኡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የኦሮሞዎችን ንቅናቄ ሌላው መደገፍ እንዳለበት ያስጠነቅቃሉ።

ይህ አይነት አቀራረብ በጣም አደገኛ አቀራርብ ነው። የኦሮሞ ብሄረተኞች አቶ ተስፋዬ እንዳሉት፣ የኦሮሚያ ትላልቅ ከተሞችን ሳያቅፉ ፣ ሌላውን ማህበረሠብ አግለው ለብቻው የሚያመጡት ዉጤት ይኖራል ብዬ አላስብም። ላለፉት ሁለት ወራት የተደረጉት እንቅሥቃሴዎች ለውጥ ካላመጡ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ነው ለዉጥየሚያመጣው ? መቼም የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን እንዲሰረዝ ተደርጓል የሚል መልስ አይቀርብም። ማስተር ፕላኑ በሌላ መልኩ መተግበሩ ስለማይቀር።

ይህ የተጀመረውና በጣም መቅዛቀዝ እየታየበት የመጣው የኦሮሞዎች እንቅስቃሴ በቶሎ ሌሎችን ባቀፈ መልኩ እንዲሰፋ ካልተደረገ ፣ በዚህ ረገድ የኦሮሞ ልሂቃን መሰረታዊ የሆነ የአካሄድ ለውጦችን ካላሳዩ፣ በጣም ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው የሚሠራው። ሌሎችን ማስጠንቀቅና በሌሎች ላይ መዛት ሳይሆን፣ የሌሎች ጥያቄ ምንድንነው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ሌላው ማህበረሰብ እኮ ላለፉት 25 አመታት በኦሮሚያ ዉስጥ ሲፈናቀል፣ ሲገደል፣ ኦሮሞ አይደለህም ተብሎ ከሥራ ሲባረር ..የነበረ ማህበረሰብ ነው። ብዙ ግፍ የተፈጸመበት ነው። ይህ ማህብረሰብብ ቢፈራና ቢጠራጠር በጭራሽ ሊወቀስ አይገባውም።

የኦሮሞ ልሂቃን "ኦሮሚያ፣ ኦሮሚያ.." የሚሉትን አቁመው፣ ጥያቄው የመብት፣ የፍትህ ጥያቄ ነው በሚል ለምን በኢትዮጵያ የዜጎችን ጥያቄ የሚያከበር ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲገነባ አይነሱም? የኦሮሞ መሬት ተወሰደ ከሚሉ (መሬቱ የሌሎች ያለሆነ ይመስል) ለምን ገበሬው የመሬት ባለቤት ይሁን አይሉም ? ለምን ምሬት ላራሹን በይፋ አይደገፉም ? የዲሞክራሲ ስርዓት ከተገነባ ፣ ሕዝቡ ከፈለገ በአጼ ሃይለስላሴ ጊዜ የነበረው አወቃቀር፣ ከፈለገ አሁን ያለው አወቃቀር፣ ከተፈለገም ደግሞ ሌላ አዲስ የመንግስት  አወቃቀር ጠረቤዛ ላይ ቀርቦ በስምምነትና ሰጥቶ በመቀበል ፣ ሕዝብ እንዲወያይበት ተደርጎ ለምን አይወሰነም ? ለምን ኦሮሚያ ወይንም ሞት የሚልአቋም ይያዛል ? ኦሮሚያ መኖር አለበት ካሉ በኦሮሚያ ዉስጥ መሆን የማይፈለገውስ ማህበረሰብ ? 75% የሚሆነው የአዳማ ህዝብ፣ 90% የሚሆነው የአዲስ አበባ ህዝብ፣ 60% የሚሆነው የጂማ ህዝብ፣ ከ 80% በላይ የሚሆኑት የቢሾፍቱና የሻሸመኔ ነዋሪዎች ….?

ይልቅ የሚያዋጣው ግትርነት ሳይሆን ነገሮችን በርጋታ ተመልክቶ፣ የሁሉንም መሰረታዊ ጥያቄ በመለሰ መልኩ መግባባቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው። ለዚህም በዋናነት ቁልፍ ሥራ መስራት ያለባቸው የኦሮሞ ልሂቃን ናቸው። ሌላው ማህበረሰብ በኦሮሞ አክራሪዎች ላለፉት 25 ሲገፋ የነበረ ነው። ይሄንን ሕዝብ ማቀፍ የግድ ያስፈልጋል።ሌላው ይቅር በኦሮሚያ ያሉትን ትላልቅ ከተሞች ማቀፍ ያስፈለጋል። በኦሮሚያ ያሉ ትላልቅ ከተሞች ደግሞ multi-ethnic ናቸው።

ግርማ ካሳ